# ማስታወቂያ

## በዲያስፖራ መኖሪያ ቤት ልማት ፕሮግራም ለመመዝገብ ለምትፈልጉ በሙሉ፤

በቻይና እና ኤምባሲያችን በሚሸፍናቸው አከባቢው አገሮች (በቬትናም፣ በማሌዥያ፣ በሲንጋፖር፣ በካምቦዲያ፣ በሞንጎሊያ፣ በሰሜን ኮሪያ፣ እና በላኦስ ሪፐብሊክ) የምትኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በሙሉ የኢፌዲሪ መንግሥት የውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር የበለጠ ለማጠናከር በሚያደርገው ጥረት የዲስፖራ መኖሪያ ቤት ልማት ፕሮግራም ተቀርፆ በሁሉም ክልሎች እና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

የፕሮግራሙ ማስፈፀሚያ መመሪያና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ዝግጅቶችን ባጠናቀቁት በትግራይ፣ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ በጋምቤላ፣ በሐረሪና በሶማሌ ክልሎች፣ እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ምዝገባ እንዲጀመር ተወስኗል፡፡ በመሆኑም በኤምባሲዎችን አማካይነት ምዝገባ እንዲከናወን በኢፌዲሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል መመሪያ ተላልፏል፡፡ በዚሁ መሠረት ከሰኔ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ምዝገባው የሚጀምር መሆኑን እየገለጽን፣ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ክልሎች በማህበር በመደራጀት የመኖሪያ ቤት መሥራት የምትፈልጉና ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ለምዝገባ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች የሚታሟሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከላይ ከተጠቀሰው ቀን ጀምሮ በኤምባሲያችን በአካል በመቅረብ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

ለበለጠ ማብራሪያ፡- 00861065327905 በመደወል ተጨማሪ ማብራሪያ ማግኘት የሚቻል መሆኑን እየጠቆምን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ እንዲሁም የአፋርና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መመሪያዎች ተጠናቆ ያልደረሱን በመሆኑ በምዝገባው ያልካተቱ ሲሆን ዝግጅቱ ተጠናቆ ሲደርሰን የምናሳውቅ መሆኑን እንጠቁማለን፡፡

**1/ለምዝገባ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣-**

በግል ተመዝግበውም ሆነ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ተደራጅተው ቤት ለመገንባት ፍላጎት ያላቸው በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

1. የፀና ፓስፖርት ቅጂ፣
2. የሚኖርበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ ወይንም ትውልድ ኢትዮጵያውያን ደግሞ የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣
3. ያገባ ከሆነ/ች ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን፣
4. ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶግራፎችን፣
5. ለምዝገባው የተዘጋጁ ቅፆችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣
6. ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም በመረጡበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ የሌለው ወይንም ኖሮት ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
7. የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በውጭ ምንዛሪ (በዶላር፣ በዩሮ፣ በፓውንድ) የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚያስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲሰጥ ቀሪውን 50% ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሆነ፣
8. የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በውጭ ምንዛሪ አገር ውስጥ በባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ፣

2/ የባንክ ሂሳብ አከፋፈት

- በቤት ልማት ፕሮግራሙ መሳተፍ የምፈልግና መስፈርቱን የሚያሟላ ዲያስፖራ በአገር ቤት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የውጭ ምንዛሪ አካውንት እንዲከፈትለት ለዚህ የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልተው ለኤምባሲችን ያሰረክባል፣ (ቅፁን ከኤምባሲያችን ጽረገፅ ማግኘት ይቻላል)፣
- ኤምባሲው የተሞላውን ፎርም ለንግድ ባንክ በመላክ ባንኩ አካውንት እንዲከፈት ያደርጋል፣ ባንኩ አካውንት ከፍቶ ለኤምባሲው ሲያሳውቅ ኤምባሲው ደግሞ መረጃውን ለግለሰቡ ያሳውቃል፣
- ግለሰቡ በተከፈተለት አካውንት ለሚመርጡት መኖሪያ ቤት ከሚጠበቅበት ገንዘብ መጠን 50 ከመቶ በውጭ ምንዛሪ ገቢ አድርጎ ደረሰኙን ይዘው በኤምባሲው በመቅረብ ይመዘገባል፣

3/የክልሎች የቤት አይነትና የዋጋ ዝርዝር መረጃ፣

1/የትግራይ ክልል

| የተ.ቁ | የግንባታው አይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | ቤቱ የሚያርፍበት ቦታ ስፋት | የግንባታው ግምት (በብር) | የማህበር አባላት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በG+2 እና ከዚያ በላይ አፓርትመንት | ባለ2 መኝታ | 74 ካ.ሜ | 424,390.00 | ከ16-24 |
| | | ባለ3 መኝታ | 100 ካ.ሜ | 573,500.00 | |
| | | ባለ4 መኝታ | 136 ካ.ሜ | 779,960.00 | |

2/የኦሮሚያ ክልል

| የተ.ቁ | የግንባታው አይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | ቤቱ የሚያርፍበት ቦታ ስፋት | የግንባታው ግምት (በብር) | የማህበር አባላት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አፓርታማ | ባለ2 መኝታ | 80 ካ.ሜትር | 400,000.00 | ከ12-24 |
| | | ባለ3 መኝታ | 100 ካ.ሜትር | 550,000.00 | |
| | | ባለ4 መኝታ | 110 ካ.ሜትር | 700,000.00 | |
| 2 | G+1ና G+2 ታውን ሀውስ | ባለ3 መኝታ | 120 ካ.ሜትር | 800,000.00 | ከ12-24 |

ማሳሰቢያ፡-

- የቤቶች ግንባታ ዋጋ የማጠናቀቂያ ሥራ ወጪን (Finishing Cost) አይጨምርም፣
- የተጠቀሰው የግንባታ ወጪ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ላይ ተመርኩዞ ሊጨምር ወይንም ሊቀንስ ይችሏል፣
- ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ሆኖ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ውስጥ ነዋሪ የሆነና በአሁኑ ጊዜ ዲያስፖራ ሆኖ ውጭ አገር የሚኖር፣

3/የአማራ ክልል

| የተ.ቁ | የግንባታው አይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | ቤቱ የሚያርፍበት ቦታ ስፋት | የግንባታው ግምት (በብር) | የማህበር አባላት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | G+4 አፓርታማ | ባለ2 መኝታ | 80ካ.ሜትር | 424,390.00 | 14 |
| | | ባለ3 መኝታ | 100 ካ.ሜትር | 573,500.00 | |
| | | ባለ4 መኝታ | 136ካ.ሜትር | 779,960.00 | |
| 2 | G+2 (ታውን ሀውስ) | ባለ3 መኝታ | 114 ካ.ሜትር | 693,120.00 | 14 |
| | | ባለ4 መኝታ | 150 ካ.ሜትር | 912,000.00 | |

**4/የደቡብ ክልል**

| ተ.ቁ | የግንባታው አይነት | | የመኝታ ቤት ብዛት | ቤቱ የሚያርፍበት ቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት (በብር) | የማህበር አባላት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መሪ ከተማ (ሐዋሳ) | G+4 አፓርታማ እና በላይ አማራጭ | ባለ2 መኝታ | 50 ካ.ሜትር | | 12 |
| | | | ባለ3 መኝታ | 65 ካ.ሜትር | | |
| | | | ባለ4 መኝታ | 80 ካ.ሜትር | | |
| 2 | ከፍተኛ የከተማ አስተዳደር ከተሞች (አርባ ምንጭ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ዲላ፣ ሆሳዕና) | G+3 አፓርታማ እና በላይ አማራጭ | ባለ2 መኝታ | 55 ካ.ሜትር | | 10 |
| | | | ባለ3 መኝታ | 70 ካ.ሜትር | | |
| | | | ባለ4 መኝታ | 85 ካ.ሜትር | | |
| 3 | መካከለኛ የከተማ አስተዳደር ከተሞች (ወልቂጤ፣ ቡታጂራ፣ ሚዛን አማን፣ ቴፒ፣ ይርጋለም)፣ | G+2 ታውን ሀውስ | ባለ2 መኝታ | 60 ካ.ሜትር | | 10 |
| | | | ባለ3 መኝታ | 75 ካ.ሜትር | | |
| | | | ባለ4 መኝታ | 90 ካ.ሜትር | | |
| 4 | ታዳጊ የከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤት ከተሞች፣ (ወራቤ፣ ሀላባ፣ ቡዲቲ፣ አረካ፣ ዱራሜ፣ ቦንጋ፣ ሳውላ፣ ጂንካና ታርጫ)፣ | G+0 አፓርታማ | ባለ2 መኝታ | 65 ካ.ሜትር | | 10 |
| | | | ባለ3 መኝታ | 80 ካ.ሜትር | | |
| | | | ባለ4 መኝታ | 95 ካ.ሜትር | | |

**5/የሶማሌ ክልል**

| የተ.ቁ | የግንባታው አይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | ቤቱ የሚያርፍበት ቦታ ስፋት | የግንባታው ግምት (በብር) | የማህበር አባላት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ክልሉ ዋና ዋና ከተሞች አፓርታማ | ባለ2 መኝታ | 74 ካ.ሜትር | 424,390.00 | 12 |
| | | ባለ3 መኝታ | 100 ካ.ሜትር | 573,500.00 | |
| | | ባለ4 መኝታ | 136 ካ.ሜትር | 779,960.00 | |
| 2 | በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች ታውን ሀውስ | ባለ3 መኝታ | 114 ካ.ሜትር | 693,120.00 | 12 |
| | | ባለ4 መኝታ | 150 ካ.ሜትር | 912,000.00 | |

**6/የሐረሪ ክልል**

| የተ.ቁ | የግንባታው አይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | ቤቱ የሚያርፍበት ቦታ ስፋት | የግንባታው ግምት (በብር) | የማህበር አባላት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አፓርታማ | ባለ2 መኝታ | 74 ካ.ሜትር | 424,390.00 | 12 |
| | | ባለ3 መኝታ | 100 ካ.ሜትር | 573,500.00 | |
| | | ባለ4 መኝታ | 136 ካ.ሜትር | 779,960.00 | |
| 2 | G+2 ታውን ሀውስ | ባለ3 መኝታ | 114 ካ.ሜትር | 693,120.00 | 12 |
| | | ባለ4 መኝታ | 150 ካ.ሜትር | 912,000.00 | |
| 3 | G+2 ታውን ሀውስ (የክልሉን ባህላዊ ኪነ ህንፃ ጥበብ ያማከለ | ባለ6 መኝታ | 181.18 ካ.ሜትር | 1,101,574.00 | 12 |
| 4 | G+1 ታውን ሀውስ (የክልሉን ባህላዊ ኪነ ህንፃ ጥበብ ያማከለ | ባለ4 መኝታ | 129.63 ካ.ሜትር | 788,150.00 | |
| | | ባለ7 መኝታ | 247.55 ካ.ሜትር | 1,505,104.00 | |

**7/የጋምቤላ ክልል**

| የተ.ቁ | የግንባታው አይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | ቤቱ የሚያርፍበት ቦታ ስፋት | የግንባታው ግምት (በብር) | የማህበር አባላት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በክልሉ ዋና ከተማ G+4 እና ከዚያ በላይ አፓርታማ | ባለ2 መኝታ | 74 ካ.ሜትር | 424,390.00 | 12 |
| | | ባለ3 መኝታ | 114 ካ.ሜትር | 693,120.00 | |
| | | ባለ4 መኝታ | 150 ካ.ሜትር | 912,000.00 | |
| 2 | በዞን ዋና ዋና ከተሞች G+2 ታውን ሀውስ | ባለ3 መኝታ | 114 ካ.ሜትር | 693,120.00 | 12 |
| | | ባለ4 መኝታ | 150 ካ.ሜትር | 912,000.00 | |

**8/የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር**

| የተ.ቁ | የግንባታው አይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | ቤቱ የሚያርፍበት ቦታ ስፋት | የግንባታው ግምት (በብር) | የማህበር አባላት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | G+4 አፓርታማ | ባለ2 መኝታ | 128 ካ.ሜትር | 582,400.00 | 14 |
| | | ባለ3 መኝታ | 160 ካ.ሜትር | 728,000.00 | |
| | | ባለ4 መኝታ | 200 ካ.ሜትር | 910,000.00 | |